# ሟርቱም መዘላበዱም ይብቃችሁ

ሳምራዊት /ከሻሸመኔ/

ኢትዮጵያን የሚመታው ቸነፈርና የምግብ እጥረት ችግር በየአስርት አመታት ኡደት የመደጋገም ባሕሪ የታየበት ነው፡፡ የእነዚህ በየአስር አመት ኡደት አገሪቱን ሲመታ የቆየው ረሐብ አንድና ተመሣሣይ መነሻ ያለው ነው፡፡ ይህም የአየር ንብረት መዛባት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ያስከተለው የዝናብ እጥረት ነው፡፡ ዘንድሮም ከ6 ሚሊዬን በላይ ኢትዮጵያውያን ለረሐብ መጋለጣቸውን መንግስት ይፋ አድርጓል፡፡ የዚህም የምግብ እጥረት መነሻ ባለፈው አመት የበልግ የእርሻ ወቅት የተከሠተው የበልግ ዝናብ እጥረት እና ሠኔ ላይ መጣል የነበረበት ክረምት ዘግይቶ ሐምሌ ላይ መግባቱ፣ እንዲሁም መስከረም ማገባደጃ ላይ መውጣት ሲኖርበት ይህ ሳይሆን በመስከረም መጀመሪያ ላይ ክረምቱ ፈጥኖ መውጣቱ ያስከተለው ችግር ነው፡፡

ዘንድሮ በኢትዮጵያ የተከሠተውን ረሐብ አስመልክቶ የረድኤት ድርጅቶች እና ሌሎች አገሪቱ የገጠማትን ችግር እናውቃለን የሚሉ ግለሠቦች የተለያየ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ የረድኤት ድርጅቶች የዘንድሮው ረሐብ የተረጂዎች ቁጥር መንግስት በይፋ እንደገለፀው 6.2 ሚሊዮን ሳይሆን ከዚያ በላይ ሊያሻቅብ እንደሚችል ነግረውናል፡፡ የችግሩን ሥፋትም በተመለከተ፣ የምግብ አጥረት ችግሩ እርዳታ በወቅቱ ከቀረበ በተረጂዎቹ ላይ ሞትና መፈናቀል ሣያስከትል በቁጥጥር ስር ሊውል የሚችል መሆኑን መንግስት ገልፆል፡፡ መንግሥት ይህንን የተከሰተውን የምግብ እጥረት መቋቋም አቅም እንዳለው በቅርብ ጊዜ በሚዲያ ገልጿል፡፡ በሌላ በኩል የረድኤት ድርጅቶች “አዛኝ ቂቤ አንጓቾች” የሚሊዮኖችን ሕይወት ከቀጠፈውና ከመኖሪያ ቄያቸው ካፈናቀለው የ1976/77 አስከፊ ቸነፈር ጋር በማመሣሠል (Famine) ነው በማለት ድብቅ አጀንዳቸውን ለማራመድ ሲሯሯጡ ይታያሉ፡፡

‹‹ስለአጠቃላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ትንታኔ መስጠት የሚያስችል እውቀት አለን›› ብለው የሚገምቱ አስተያየት ሠጪዎች የችግሩ መንስኤና መፍትሔውንም ሊነግሩን ሞክረዋል፡፡ ለምሣሌ በኢትዮጵያ የቀድሞ የአሜሪካ አምባሳደር ዴቪድ ሺን በአገሪቱ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከሠተው ረሃብ መንስኤ፣ የአየር ንብረት መዛባት የሚያስከትለው ድርቅ ሣይሆን፣ የአገሪቱ የመሬት ፖሊሲ መሆኑን ነው የነገሩን፡፡ መሬት የሕዝብና የመንግስት ንብረት መሆኑ ቀርቶ የሚሸጥ የሚለወጥ የግል ሐብት እንዲሆን ብታደርጉ የምግብ እጥረት ረሐብ አጠገባችሁ አይደርስም ብለውም በየአደባባዩ ሲደሰኩሩ ይደመጣሉ፡፡

ለኢትዮጵያ ባዕዳን የሆኑት የረድኤት ድርጅቶችና ሌሎች አስተያየት ሠጪዎች የሕዝቡን የመኖር ዋስትና የማረጋገጥ ኃላፊነት ካለው መንግስት የበለጠ አሳቢና ተቆርቋሪ መስለው  ነው የቀረቡት፡፡ እውነታውን ጠለቅ ብሎ ላጤነው ግን ‹‹ከተቆርቋሪዎቻችን›› መረጃና አስተያየት ጀርባ የራሳቸውን ጥቅም ያማከለ (ምናልባት የአገሪቱንና የሕዝቧን ገጽታ በሚጐዳ መልኩ) ሥውር አላማ መኖሩ ጎልቶ ይታይባቸዋል፡፡

እነዚህ የተነገሩን አደጋዎች ወይም ሥጋቶች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ እይታ ይኖረን ዘንድ ‹‹ ተቆርቁሪዎቻችን ›› ያቀረቡልንን መረጃ እና የሠጡንን አስተያየት፣ ከራሣቸው ባሕሪና ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በነገራችን ላይ እነዚህ ወገኖች ኢትዮጵያ የሚገጥማትን ችግር በተመለከተ በመንግስት ከሚገልፀው በላይ በእጅጉ የተጋነነ መረጃ ሲያቀርቡ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ላይ ተመሣሣይ አስተያየት ሲሠጡ የዘንድሮው የመጀመሪያ አለመሆኑ መታወስ አለበት፡፡

የረድኤት ድርጅቶቹ የዘንድሮውን የምግብ እርዳታ ፈላጊዎች በመንግሥት ከተገለፀው 6.2 ሚሊዮን ወደ 12-13 ሚሊዬን፤ የችግሩን አስከፊነት ደረጃም ከምግብ እጥረትነት ይልቅ ቸነፈር ነው በሚል ያቀረቡትን እጅግ የተጋነነ መረጃ ስንመለከት፣ በቅድሚያ አንድ እውነታን ማስታወስ ይኖርብናል፡፡ ይህም የኢፌዲሪን መንግስት፣ ሕዝብ በውክልና ሥልጣን ሲሠጠው ሕልውናውን የማስጠበቅ ላፊነትና

ተጠያቂነትንም የተጣለበት መሆኑ ነው፡፡ ታዲያ እነዚህ የዕርዳታ ድርጅቶች በአገራችን የተከሰተውን የምግብ እጥረት በኃይል በማንጠራራት የራሳቸውን ድብቅ አጀንዳ ለማራገብ ሲሯሯጡ ይታያሉ፡፡

በመሆኑም መንግስት፣ ‹‹ተቆርቋሪዎቻችን›› በጠነቆሉት የዘንድሮ ‹‹ ችነፈር ›› ለረሃብ የተጋለጡ የምግብ እርዳታ ፈላጊዎች ቁጥር በግማሽ ቀንሶ 6.2 ሚሊዮን ብቻ ነው በማለት፣ ከዜጎቹና ከአለም እውነታውን ቢደብቅ፤ የምግብና የመድሃኒት እጥረት ሲከሰት ተጐጂው ማን እንደሆነ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በሐቅ ላይ የተመሠረተ መረጃ ለህብረተሰቡም ሆነ ለአለም አቀፍ መንግሥታት አሳውቋል፡፡ ባለፉት መንግሥታት እንደታየው ተረጂዎች ጎዳናዎች ላይ መባቸውን አንጥፈው፣ አኮፋዳቸውን አንግተው ከተሜውን የሚላስ የሚቀመስ እየለመኑ ችግሩን ይፋ ማውጣታቸው እንደማይቀር፣ በ1966 እና 1976/77 ረሐብ ማስታወስ በቂ ነው፡፡ መንግስት ችግሩን መደበቁ እንደሚያስጠይቀውም ያውቀዋል፡፡ ይህ እውነታ ምንም የሕግ ኃላፊትና ተጠያቂነት የሌለባቸው ባእዳን፣ በደረሠብን ችግር ከመንግሥት በላይ ተቆርቋሪና ተከራካሪ ያደረጋቸው ስውር ኢላማ አላቸው የሚለውን ግምት ያጠናከረዋል፡፡

አንደኛውና ዋነኛው አላማቸው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከሁለት ሳምንት በፊት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቀርበው፣ የፕሬዚደንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ የፓርላማውን የ5ኛ አመት የስራ ዘመን መክፈቻ ንግግር ላይ ከም/ቤቱ አባላት ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጡ የገለፁት ነው - የእርዳታው ኢንዱስትሪ፡፡ ይህም በአለም አቀፍ የእርዳታ ሥርአት ውሰጥ፣ የእርዳታውን ፈንድ ከሚያሠባስቡ፣ እርዳታውን ለተረጂዎች ከሚያቀርቡና ከሚያሠራጩ፣ የረድኤት ድርጅቶች በተጨማሪ ለትርፍ አላማ የተቋቋሙ አምራች፣ የግዢና የትራንስፖርት ግዙፍ ኩባንያዎች ይሣተፋሉ፡፡ ጠ/ሚሩ የእርዳታ ኢንዱስትሪ ያሉት እነዚህን በእርዳታው ሒደት ውስጥ የሚሣተፉ፣ ለትርፍ አላማ የተቋቋሙ ኩባንያዋች ነው፡፡ የተረጂዎች ቁጥር መጨመር፣ በእርዳታ የሚቀርበው ምርት አምራች ሻጮች የትራንስፖርት ኩባንያዋች የምርትና የአገልግሎት ሽያጭ በማሣደግ ትርፋማነታቸውን ይጨምራል፡፡ በመሆኑም የእርዳታ ፈላጊዎችን ቁጥር መብዛት ለእነሡ ሲሳይ

ነው - የመአት ወርዷል ሟርታቸው መነሻም ይሔው ነው፡፡ የእርዳታውን ኢንዱስትሪ ትርፋማነት አራጋቢ ድርጅቶችና ግለሠቦች ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመሸፋፈን በሃገራችን የተከሰተውን የምግብ እጥረት በማጦዝ መአት በህዝባችን ላይ እንደወረደ በመለፈፍ በተረጂዎች ሥም ትርፍ ለማጋበስ ሲሯሯጡ ይሥተዋላሉ፡፡ ይህ ማለት በአገራችን አንዳንድ ቦታዎች በዝናብ እጥረት ምክንያት የምግብ እጥረት አልተከሰተም አይደለም፤ ነገር ግን በተከሰተብን የዝናብ እጥረት ምክንያት ጊዜያዊ ችግር ቢገጥመንም በሃሰት መረጃ ለሌሎች ጥቅም ማጋበሻ መሣሪያ መሆን የለብንም፡፡

ሌላው የሚገርመው ነገር ዘንድሮ ከተከሠተው የምግብ እጥረት ችግር ጋር በተያያዘ የችግሩ መነሻ ምክንያትና መፍትሔ ተብሎ የቀረበው አስተያየት ነው፡፡ ይህም ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከሠት ረሐብና የምግብ እጥረት ችግር ጋር በተያያዘ ብቻ ሣይሆን፣ አጠቃላይ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ችግር እንደሆነ ተደርጎ በተደጋጋሚ ሲነገረን የቆየው አገሪቱ የምትከተለውን የመሬት ፖሊሲ የሚመለከት ነው፡፡ አስተያየት ሠጪዎቹ ‹‹ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከሠት የረሐብ ችግር መንስኤ፣ መሬት በሕዝብና መንግሥት ይዞታ ሥር መሆኑ ነው፣ የችግሩ ዘላቂ መፍትሔም ሊሆን የሚችለው መሬት መሸጥ መለወጥ ሲቻልና ወደ ግል ይዞታነት ሲለወጥ ብቻ ነው›› ባዮች ናቸው፡፡

የምግብ እጥረት የኢትዮጵያ ብቻ ችግር ሣይሆን፣ ተመሣሣይ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙ አገራትም ይጋሩታል፡፡ ከእነዚህ መካከል ለኢትዮጵያ የረሐብ ችግር እንደመንስኤ ከቀረበው የመሬት ፓሊሲ የተለየና መሬትን መሸጥ መለወጥ እንዲቻል የሚፈቅድ ፖሊሲ ያላቸውም ጭምር ይገኙበታል፡፡ የዘንድሮውን ረሐብ እንኳን ብንወስድ ከኢትዮጵያ በተጨማሪ ሠባት የአፍሪካ ቀንድ አገራትን - ለምሳሌ ኬንያ ፣ ታንዛኒያ፣ ሶማሊያን አጥቅቷል፡፡ ከእነዚህ መሃከል ኬንያን ብንመለከት የምትከተለው የመሬት ፖሊሲ፣ መሬት የግል ንብረት እንዲሆን የሚፈቅድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እንግዲያው ለኢትዮጵያ የረሐብ ችግር እንደ መፍትሔ ያቀረበውን ፖሊሲ የምታስፈጽመውንና፣ ከኢትዮጵያ ጋር ተቀራራቢ የኢኮኖሚ አቅም ያላት የኬንያ የረሃብ ምንጭስ ምን ይሆን?

በሌላ በኩል ቻይና ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ መሬት በመንግስትና በሕዝብ ይዞታ እንዲሆን ያደረገ ፖሊሲ ስትከተል ነው የቆየችው፡፡ አሁን የደረሠችበት የአለምን ገበያ በበላይነት ለመምራት ያስቻላት የእድገት ደረጃ ላይ የደረሠችውም፣ ይህንኑ የመሬት ይዞታ ፖሊሲ ባስፈፀመችባቸው አመታት መሆኑም መዘንጋት የለበትም፡፡ ከላይ ለአብነት ያህል የተጠቀሡት የሁለቱ አገሮች እውነታ፣ አሁን ኢትዮጵያ የምትከተለው የመሬት ፖሊስ ፣ አገሪቱን በተደጋጋሚ ከመታው ድርቅና ይህ ካስከተላቸው ረሃብ እንዲሁም ቀጣይ የኢኮኖሚ እድገቷን ከማረጋገጥ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለው ያመላክታል፡፡

እንግዲህ ከዚህ እውነታ ብንነሳ እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ የምግብ እጥረት ሊከሰት የቻለው ተግባራዊ ባደረገችው የመሬት ፖሊሲ ሊሆን አይችልም፡፡ ይልቁንም ኢትዮጵያ እየተገበረችው ያለው የመሬት ፖሊሲ ልማትን ሊያፋጥን፣ ኢንቨስትመንትን ሊስብ የሚችል መሆኑ እየታወቀ የእርዳታ ኢንዱስትሪው አራጋቢዎች ጥቅም ለማጋበስ ሲሉ የሃሰት መረጃን በመንዛት የሃገራችንን ገፅታ ለማበላሸት ሲጥሩ ይታያሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ለግብርና ተስማሚ ከሆነ 74 ሚሊዮን ሄክታር ያህል መሬት ውስጥ እስከ አሁን 85% ያህሉ በገጠር የሚኖር አርሦ አደር ሠፍሮበት የለማው 11 ሚሊዮን ሄክታር ወይም 15 % ገደማ ነው፡፡ መንግስት ሠፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት ላይ መሠማራት ለሚፈልጉ ባለሐብቶች ከዚህ መሬት ላይ በአነስተኛ የሊዝ ዋጋ እንዲያገኙ እያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም በሠፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት ላይ የሚሠማሩ ባለሐብቶች መሬት እንዲያኙ አርሦ አደሩ አሁን የሚጠቀምበትን መሬት እንዲሸጥ የሚያስገድደው ተጨባጭ ምክንያት የለም፡፡ አርሦ አደሩ መሬቱን ይሸጥ እንኳን ቢባል ለሠፋፊ የእርሻ ልማት የሚያስፈልጉትን በሺዎች ሄክታር የሚለካ መሬት ለማግኘት፣ ኩታ ገጠም መሬት ያላቸው በሺዎች የሚቆጠሩ አርሦ አደሮች በአንድ ጊዜ መሬታቸውን ለመሸጥ መስማማት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ በተአምር ካልሆነ በስተቀር ይሆናል ብሎ ማሠብ የዋህነት ነው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ መሬት የሕዝብና የመንግስት ይዞታ ሥር ያለ የማይሸጥ የማይለወጥ ሐብት መሆኑ አርሦ አደሩ መሬቱን ሸጦ በሌላ ሥራ ላይ የመሠማራት፣ የመኖሪያ ቦታውን እንዳይቀይርና ለችግር እንዳይጋለጥ ረድቶታል፡፡ ኢትዮጵያ የመሬት መሸጥ መለወጥ ፖሊሲን ብታራምድ ኖሮ ዛሬ ከተሞቻችን መሸከም ከሚችሉ ሕዝብ በላይ ተጨናንቀው ማህበራዊ ግልጋሎት ሰጪ ተቋማት ሥራቸውን ማከናወን ይሳናቸው እንደነበር አንዳንድ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በአርሶ አደሩ የተያዘውን መሬት ስንመለከት በአንድ አርሦ አደር አባወራ ይዞታ ሥር ያለ መሬት በአማካይ ከ1-1.5 ሄክታር አይበልጥም፡፡ መንግስት ለሠፋፊ እርሻ ኢንቨስተሮች መሬት በተመጣጣኝ በሚሠጥበትና የመሬት አቅርቦት ችግር በሌለበት ሁኔታ፣ ከዚህ የሊዝ ዋጋ በላይ የአርሦ አደሩን መሬት የሚገዛ ኢንቨስተር እንደማይኖር ግልጽ ነው፡፡ አርሶ አደሩ በይዞታው ሥር ያለውን፣ አንድ ቢበዛ አንድ ተኩል ሄክታር መሬት ሸጦ በሚያገኘው ቢበዛ 10፣15 ሺህ ያህል ብር ከነቤተሠቡ ከተማ ገብቶ የመኖሪያና የሚሠራበት ቦታ ገዝቶ ወይም ተከራይቶ በሌላ ስራ ላይ በመሠማራት (ከግብርና ውጭ ሙያ የሌለው መሆኑም ሳይዘነጋ) ለዘለቄታው የተሻለ ሕይወት መምራት ይችላል ብሎ ማሠብ ተገብነት ያለው አይደለም፡፡ አርሶ አደሩ የመሬት ባለቤትነት ዋስትና ለማረጋገጥ ለሁሉም አርሶ አደሮች የመሬት ባለቤትነቱን የሚገልፅ ማስረጃ ተሰጥቶታል፡፡ ማንኛውም አርሶ አደር መሬቱን ከመሸጥ መለወጥ መለስ የፈለገውን በመሬቱ ላይ ማልማት፣ በየጊዜው በሚታደስ ውል ለፈለገው ማከራየት (ማኮናተር) እንዲችል ሁኔታዎች ተመቻችተውለታል፡፡

በአጠቃላይ ፣ ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች፣ የኢትዮጵያ  የመሬት ፖሊሲ ፣ በአገሪቱ ለተከሠቱ የምግብ እጥረት ላይ ያስከተለው አንድም አሉታዊ ተጽእኖ የለም፡፡ እንዲያውመ በተግባር እንደሚታየው የኢትዮጵያ የመሬት ፖሊሲ ባለፉት ተከታታይ ስድስት አመታት የተመዘገበው ከ10% በላይ የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ የምግብ እጥረት ችግሩ መንስኤ፣ የአርሦ አደሩ የግብርና ሥራ በዝናብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የአየር ንብረት መዛባት ሲያጋጥም ይህንን

መቋቋም ባለመቻሉ ነው፡፡ መንግስትም ይህን ተገንዝቦ ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት አነስተኛ የመስኖ ልማት መሠረተ ልማቶችን በመገንባት፣ አርሶ አደሩ በዝናብ ውሃ ላይ ጥገኛ በመሆኑ የተፈጠረውን ችግር ተቋቁሞ የምግብ ፍላጎቱን የሚያሟላ ምርት የሚያገኝበትን ፖሊሲ ቀርጾ እየተንቀሳቀሠ መሆኑን የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትር መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል፣ በክልሉ ፕሬዚደንት አቶ አባዱላ ገመዳ የግሉንና የመንግስት ሚዲያ ጋዜጠኞች በተገኙበት የጎበኙት የአዋሽ ወንዝ በመጥለፍ 18 ሺ ሔክታር መሬት ማልማት የሚያስችለው የፈንታሌ የመስኖ ቦይ መሠረት ልማት ለዚህ አስረጂነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

አሁን የተከሠተውን የምግብ እጥረት ችግር ለመቋቋምም፣ አስቸኳይ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች የሥነ ልቦና ጉዳት ሣይደርስባቸው ባሉበት ቦታ እርዳታውን እንዲያገኙ ከማድረግ በተጨማሪ፣ በሚቀጥሉት ጊዜያት ችግሩን በዘለቄታው የሚፈቱ አነስተኛ የመስኖ ልማት ሥራዎችን መንግሥት በማከናወን ላይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ሰፊ የውሃ ሃብት ባለቤት በመሆኗ በአርሶ አደሩ ሊለሙ የሚችሉ አነስተኛ የመስኖ ሥራዎችን ለማካሄድ መንግስት ጥረት እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡ ይህ ሲሆን ነው ግብርናው ከዝናብ ጥገኝነት ሊላቀቅ የሚችለው፡፡

በአጠቃላይ የረድኤት ድርጅቶችና የኢትዮጵያውያን ችግር እናውቃለን ባዮቹ አስተያየት ሠጪዎች፣ የራሣቸውን መበልፀጊያ መንገድ ለማመቻቸትና፣ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ካለመገንዘብ፣ ወይም ለመገንዘብ ካለመፈለግ የመነጨ ሟርት ነው፡፡ ሟርቱም መዘላበዱም ይብቃችሁ፡፡